# ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 5 ቁጥር 1 ጥቅምት ፳፰ ቀን ፪ ሺህ ፲ ዓ.ም.

## ለፈራጅ ፍርድ ይስጠው!

*(የጎጃሙ ገዳይ መቶ አለቃ እሸቱ አለሙ ፍርድ ሂደት ምክንያት በማድረግ)*

ኅዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም. በፍየል ወጠጤና በወታደራዊ ማርሽ አጃቢነት የቀድሞ አፄ ኃ/ሥላሴ ባለሥልጣናትን ያለፍርድ የረሸነው ደርግ የየዕለት ዜናው ተረሸኑ፣ ተገደሉ፣ ተደመሰሱ፣ እርምጃ ተወሰደባቸው ወዘተ. ለመሆኑ በየቀኑ ይወጡ የነበሩ "አዲስ ዘመን" እና "የዛሬይቱ ኢትዮጵያ" ጋዜጣን ማገላበጥ በቂ ነው።

ፋሽስታዊው ደርግ በ17 ዓመት የአፈና አገዛዙ መደምደሚያ ያደረገው ፋሽስቱ መንግስቱ ኃ/ማርያም ከመፈርጠጡ በፊት በ1981 ዓ.ም. ግንቦት 8 መፈንቅለ መንግስት ተገን በማድረግ በተጠናወተው ገዳይ በትሩ የረሸናቸው ጄነራሎቹ የመጨረሻው ነበሩ። ያለፍርድና በጭካኔ ሲገድል ጀምሮ፣ ሲገድል ቀጥሎ፣ ሲገድል ያበቃለት ፋሽስታዊ አገዛዝ በሀገራችን ኢትዮጵያ ቢኖር የደርግ ኢሠፓ (የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ) ዘመን ነበር።

ፋሽስቱ መንግስቱ ኃ/ማርያምና የደርግ ኢሠፓ ገዳዮች ያለፍርድ ርሸና ከአካሄዱበት ወቅትና ዕለት ጀምሮ ማስፈራራትን፣ ማሸማቀቅን፣ ማስበርገግን፣ ማሸበርን፣ በጥቅል አጠራሩ "ቀይ ሽብር"ን እንደጀመሩት 60ዎቹ በመባል በሚታወቀው የብ/ጄ አማን ሚካኤል አንዶምን ጨምሮ የአፄ ኃ/ሥላሴ ባለስልጣናት ግድያ በቂ ማስረጃ ነው። ለአብነት ያህል ከደርግ አባላት ውስጥ እነ ሻምበል ኪሮስ ዓለማየሁ፣ በ1968 ዓ.ም. መጨረሻ ሻለቃ ሲሳይ ሀብቴ፣ ብ/ጄነራል ጌታቸው ናደውና ሌሎች፣ ከወቅቱ የተማሪው እንቅስቃሴ አካላት ውስጥ መጋቢት 9 ቀን 1967 ዓ.ም. የተገደሉት እነ መለስ ተክሌ፣ ረዘነ ኪዳኔ፣ ግደይ ገብረዋህድ እና የኦሮሞ ነጻነት ድርጅት መሪ ተብለው የተረሸኑት ብርጋዲር ጀነራል ታደሰ ብሩ… መችና እንዴት እንደተገደሉ የታሪክ ማህደርን ማገላበጡ በቂ ነው። ሌላ እንጨምር፤ ጦር ፍርድ ቤት ቀርበው የተለያየ ጊዜ እስር የተፈረደባቸውን ሕግ ጥሶ ግንቦት 30 ቀን 1967 ዓ.ም. ወታደር ጌታቸው ፋንታ፣ አቶ ክፍሌ ሞገስ፣ አቶ ወርቁ ሥዩም፣ አቶ ዘሩ ኃይሌ እና አቶ እንድሪስ ኪያር የረሸነ ደርግ እውን እነኚህ ከ"ቀይ ሽብር" በፊት የነበሩ ፍጅቶች የማሸበር አካሉ አይደሉምን?

በፋሽስታዊ ጭካኔው የሂትለር ታናሽ ወንድም መንግስቱ ኃ/ማርያም በጥር 26 ቀን 1969 ዓ.ም. በደርጉ ውስጥ መለስተኛም ቢሆን የለውጥ አንቀሳቃሽ ሊሆኑ የሚችሉ የደርግ አባላትን ሊቀመንበሩን ብ/ጄነራል ተፈሪ በንቲን ጨምሮ ወደ ሰባት የሚጠጉ ወታደራዊ ሹማምንትን የበላ ጨካኝና አረመኔ ነው። መንግስቱ ኃ/ማርያም ከጎኑ ሆኖ ላሸረገደለት ኮ/ሌ አጥናፉ አባተ እንኳ ያልተመለሰ አረመኔ

ነው። የመንግስቱ ወዳጅ፣ ዘመድ፣ ፍቅር፣ ደስታ...ከስልጣኑ በቀር ሌላ አይታሰብም ነበርና:: ሀገር ሳይሆን ቤቱን፣ ሕዝብ ሳይሆን እራሱን ወዳድ ነበርና አንድ ትውልድ ቀብሮ በመፈርጠጥ እራሱንና ቤተሰቡን ወድዶ፣ 27 ዓመት ተገንና ጠለላ በዚምባብዌ ተሰጥቶት፣ ያፈሰሰው የያ ትውልድ ደም ትንሽም ሳይጸጽተው እንዳሻፈ ይገኛል።

የየካቲት 66ን ሕዝባዊ አብዮት አቅጣጫውን አስቶ ወደ ኢዴሞክራሲያዊና አምባገነን አገዛዝ እየተጓዘ ያለውን የደርግ ስብስብ አይዞህ ባይ ምሁራን እንደመኖራቸው ሁሉ ከሀገርና ሕዝብ ጎን ተሰልፈው ለዴሞክራሲያዊ መብትና ለጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት መመሥረት በቆራጥነት የታገሉ የኢትዮጵያ ሀቀኛ ምሁራንና ልጆች በ14ቱም ክፍለሀገራት ዘር፣ ቋንቋ፣ ክልል፣ ሃይማኖት፣ ጾታና፣ ዕድሜ ሳይገድባቸው በአንድ ኢትዮጵያዊ ቋንቋና ብሔራዊ አጀንዳ ዓላማቸውን ከፍ ያደረጉ የያ ትውልድ ጀግኖች በፋሽስቱ መንግስቱ ኃ/ማርያምና የደርግ ኢሠፓ ካድሬዎች የሰው ልጅን ጭካኔ ቋንቋ ሊገልጸው ከሚቸገረው በላይ አሰቃይተዋል፣ ዘልዝለዋል፣ ጨፍጭፈዋል፣ ገድለዋል።

ደርግ ሕዝባዊውን ተቃውሞና ትግል ለማኮላሸት ሥልጣን ኮርቻ ላይ ከተፈናጠጠበት 1967 ዓ.ም. ማግስት ጀምሮ በየቀኑ በየአካባቢው በተለይ ወጣቶችንና ተማሪዎችን በማፈስና በማሰር የሚያደርገው ማስፈራራት፤ ብቻውን እንደፈለገው በሕዝብና በሀገር ላይ ሊያጓራና ሰጥ ለጥ አድርጎ ሊገዛ እንደማያስችል የተረዱት አጃቢ ባንዳ ምሁራን ደርግን በቅስቀሳውና በመግለጫው ከመርዳት አልፈው ሕዝባዊ ትግሉን እንዴት እንደሚደመስስ ዕቅድ ዘረጉለት። የ "ቤት ለቤት አሰሳ፣ ዘመቻ መንጥር፣ ዘመቻ ደምስስ፣ ነፃ እርምጃ፣ ቀይ ሽብር" እንደቅደም ተከተላቸው ተግባራዊ ይሆኑ ዘንድ የነደፉትን ዕቅድ ግድያ ጎረቤቱ የሆነው ፋሽስት መሪ ተግባራዊ በማድረግ ትውልድ ፈጀበት። በ1968 ዓ.ም. የቤት ለቤት አሰሳ በተለይ ትኩረቱን በከተሞች አድርጎ የጀመረው "ዘመቻ መንጥር" እድገቱን እያሻሻለ ወደ ድምሰሳ ተጓዘ። በመንገድ ላይ ያገኙትን ወጣት ገድሎ በመሰወር ወደ "ነፃ እርምጃ" ተሸጋግሮ በመጨረሻ ሕፃን፣ እናት፣ አባትን ጨምሮ የሁሉንም ቤተሰብ ቤት ያንኳኳ "ቀይ ሽብር" በመላው ሀገሪቷ ተካሄደ። ***<u>የ1970ው ቀይ ሽብር ደርግ ግድያ የጀመረበት ወቅት ሳይሆን የደርግ ግድያ አንድ ትውልድ የማጥፋት ዘመቻ የመጨረሻው ደረጃ ነበር።</u>***

በሕግ የተቋቋሙበትን ዓላማና ተግባር ያሳተ ትዕዛዝና ግድያ አስፈጻሚ አካላት በከተማ "የቀበሌ ማኅበራት" በገጠር "የገበሬ ማህበራት" ሆኑ። "ዘመቻና ግድያ" መለያው የሆነው ደርግ ለዚህ ትውልድ የማጥፋት የግድያ ዕቅዱ "የአብዮታዊ ዘመቻና ጥበቃ መምሪያ" በመላዋ ሀገሪቷ መዋቅሩን በመዘርጋት ተጠሪነቱ ለፋሺስቱ መንግስቱ ኃ/ማርያም የሆነ ተቋም ተመሠረተ። በዚህ አፋኝና ገዳይ ዘመቻ መምሪያ በከተማ ከከፍተኛ እስከ ቀበሌ፣ በገጠሪቷ ኢትዮጵያ ከክፍለ ሀገር፣ አውራጃና ወረዳ አስታኮ በገዳይ ካድሬዎቹ አማካይነት መዋቅሩ በመላ ሀገሪቷ አዲስ አበባን ጨምሮ ተዘረጋ። በአንዳንድ አካባቢዎች እየተካሄደ ያለውን ግድያ ሀገር አቀፋዊ መልክ ይይዝ ዘንድ በ"ሕግ" ሽፋን አዋጅ ወጣለት። በመዋቅሩ የተሰገሰጉ መላ የደርግ አባላትና በወቅቱ የነበሩት "የኢትዮጵያ ማርክሳዊ-ሌኒናዊ ድርጅታዊ ኅብረት" (ኢማሌድኅ) በመባል የተመሠረቱት መኢሶን፣ ወዝሊግ፣ ኢጭአት፣ ማሌሪድና አብዮታዊ ሰደድን ያካተተው ኅብረት ካድሬዎችን ጨምሮ በየቀብሌው ለተቋቋሙት "የአብዮት ጥበቃ" አባላትና በገጠር ለተቋቋሙት "የገበሬ ሚልሺያ ጥበቃ" ቡድን አባላት ሙሉ በሙሉ ያለምንም ጥያቄ የመግደል መብት ተሰጠ።

በተለይ ወጣቶችና ተማሪዎችን ማዕከል አድርጎ ሕፃናትን፣ አዛውንት እናት አባቶችን ሳይለይ ለተዘጋጀው የጅምላ ጭፍጨፋ እሥር ቤቶች በየቀበሌው ከፍተኛ፣ አውራጃና ወረዳ ድረስ ተከፈቱ። ይህ ለደርግ ካድሬዎችና አብዮት ጠባቂዎች የተሠጠው ገደብ የሌለው የግድያ መብት፣ በ"አብዮታዊ

ዘመቻና ጥበቃ መምሪያ" ሽፋን የተዘረጋው የ"ቀይ ሽብር" መዋቅር ውስጣቸው በቅናት፣ በተንኮል፣ በምቀኝነት፣ መች ዕድል አግኝቼ? ባይ ቀን ጠባቂ አውሬዎችን ብቅ አደረገ። ሂደቱ ከፖለቲካው ባሻገር የሚያውቁትን በማጥቃት ላይ ሳይቀር በሰፊው ተካሄደ። ፍጅቱ በወቅቱ ተጠናክሮ ይታገል እነበረው ድርጅት "የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ" (ኢሕአፓ) ላይ ብቻ ያነጣጠረ ሳይሆን ደርግ ለሥልጣን ያሰጉኛል ያላቸውና በጥቅሉ የሕዝብ ልጆች ላይ ሆነ። የሰው ልጅ ድብቅ ባህሪ እንዳለው "ቀይ ሽብር" በርካታ ገዳዮችን አደባባይ አወጣ።

በ"ያ ትውልድ ተቋም" ድረ ገጽ (www.yatewlid.com, www.yatewlid.org ) በ"አብዮታዊ ዘመቻና ጥበቃ መምሪያ" ሥር ዋና ዋና የቀይ ሽብር ተሳታፊዎችና ገዳዮች በትንሹ ወደ 1350 ስሞች የተዘገቡ ሲሆን በገዳይነታቸው በጊዜው ገነው ከነበሩት የአራት ኪሎውን ግርማ ከበደን ጨምሮ እንደ ሻለቃ መላኩ ተፈራ (ጎንደር)፣ ገስግስ ገ/መስቀል (ሸዋ)፣ ጄ/ል ጌታቸው ሽበሺ፣ ሻለቃ አሊ ሙሳ፣ ኮ/ሌ ተካ ቱሉ፣ ሻለቃ ካሣዬ አራጋው፣ የጎጃሙ መቶ አለቃ አለሙ እሸቱ፣ የከፍተኛ 1 እርገጤ መድበው፣ የከፍተኛ 13 እሸቱ ሸንቁጤ፣ የከፍተኛ 16 ቺፍ ተስፋዬ፣ የከፍተኛ 9ኙ ቀልቤሳ ነገዎ፣ የከፍተኛ 15ቱ ከፈለኝ ዓለሙ ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው።

"ለፈራጅ ፍርድ ይስጠው" እንዲሉ በትንሹ ከዛሬ 43 ዓመት የደርግ አገዛዝ ዘመን ያለአግባብና በግፍ የፈሰሰው የኢትዮጵያ ልጆች ደም ከመቃብር በላይ እየጮኸ ነው። ወያኔ/ህወሀት ሥልጣኑን እንደተቆጣጠረ የ"ቀይ ሽብር" ተሳታፊዎችን ለፍርድ የማቅረብ ሂደትን አስታኮ በ"ነፃና ገለልተኛ" ፍርድ ቤት ጥፋታቸው ይታይ ዘንድ ተጀምሮና በቀረቡት ምስክሮችና መረጃዎች አማካይነት የተሰጠውን ፍርድ ከ"ሕግ በላይ" የሆነው ወያኔ/ህወሀት ፍርዱን ቀልብሶ ዛሬ የደርግ ገዳዮች በመጽሐፋም ዋነኛ፣ በፖለቲካውም ዳግም ተዋንያን፣ በአደረጉትም የደም ታሪካቸው ተወዳሽ መሆናቸውን ስናይ ይገርመናል። በመጠኑም ቢሆን በአጠቃላይ ለሰው ልጅ መብትና ደህንነት ተቆርቋሪ የሆኑ የውጭ ዜጎችና የፍርድ ተቋማት የእኛን የሀገራችንን የ"ቀይ ሽብር" ታሪክ እንደራሳቸው በመቆርቆርና በማየት "ውቅያኖስ በጭልፋ" ቢሆንም በስደተኛ ስም የተወሸቁ ነፍሰ በላዎችን በወቅቱ የግፍ ሰለባ በሆኑ ወገኖቻችን ጥረት አማካይነት እየታደኑ ለፍርድ ሲቀርቡ ስናይ "ለሁሉም ጊዜ አለው" እንላለን።

ቀደም ሲል የከፍተኛ 9ኙን ቀልቤሳ ነገዎ በፈጸመው ወንጀሉ በተደረገው የፍርድ ሂደት በእሥር ወደ ሀገሩ የሰደደው የአሜሪካ መንግስት በቀጣይነት የዛሬ አምስት ዓመት ገደማ የከፍተኛ 15ቱን አረመኔ ከፈለኝ ዓለሙን የ22 ዓመት እሥር ተፈርዶበት በዴንቨር እሥር ቤት እነደሚገኝ በወቅቱ መዘገባችን ይታወሳል። ይኸው ደግሞ ዛሬ፤ የዛሬ አርባ ዓመት ወንጀለኛ የጎጃሙ ገዳይ መቶ አለቃ እሸቱ አለሙ በኔዘርላንድ ዘ ሄግ ፍርድ ቤት ቀርቦ በወቅቱ በነበሩ የግፉ ሰለባዎችና ቤተሰቦች ምሥክርነት ወደ መጨረሻው የፍርድ ሂደት ላይ መሆኑ በተለያዩ የዜና አውታሮች እየተዘገበ ነው።

መቶ አለቃ እሸቱ ዓለሙን ለፍርድ በማቅረብ ሂደት ሳትታክቱ የጣራችሁና በምስክርነትም ለተሳተፋችሁ ወገኖች በሞላ በግፉ ሰለባዎች በተለይም በጎጃም ክ/ሀገር በጨፈጨፋቸው ወገኖቻችን ስም ምስጋናችንን ከ "ያ ትውልድ ተቋም" እናቀርባለን። የመቶ አለቃ እሸቱ ዓለሙ በፍርድ ሂደት ላይ መሆኑን በመዘገብ በየገጠሩ ላሉ ኢትዮጵያውያን እንዲዳረስ ላደረጋችሁ ባለሙያ ጋዜጠኞች ምስጋና ይድረሳችሁና ይህ ዜና በመቶ ሺህ የሚቆጠር ቤተሰብን "አይ ያንተ ሥራ! የአላህ! ለአንተ ምን ይሳንሃል? ሽኩራን! ተመስገን!" እንደሚያሰኝ መገመት ያስችላል።

"የ…ታ…ጋ…ይ ድምጽ ይጮሃል! ይ…ጮ…ሃ…ል ከመቃብር!" እውነት ዛሬ ጩኸታችሁ ተሰምቷል። ዛሬ ያለ ሕግ ፈራጅ በሕግ ፍርዱን አግኝቷል፣ ያለ ሕግ አሳሪ በሕግ ታስሯል። ደስ ይበላችሁ

እንላለን። "ዓይን ያለው ይይ! ጆሮ ያለው ይስማ!" ዛሬም እንላለን። የቀልቤሳ ነገዎ፣ የከፈለኝ ዓለሙ፣ የእሸቱ ዓለሙ ከ40 ዓመታት በኋላ ለፍርድ መቅረብ ትልቅ ትምህርት ሊሆን ይገባዋል። የዓመታት መርዘም ከወንጀል ነፃ አያደርግም። አካባቢ አይደለም ሀገር መቀየር ከሰሩት ወንጀል ከለላ አይሆንም። ለሕግ የበላይነትና ለሰው ልጆች "አቤት!" ባይ አካላት እስካሉ ድረስ በሰው ልጅ ላይ የተሰራ በደልና ግፍ ምንጊዜም ሕጋዊ ፍርዱን ያገኛል። እውነት ታሸንፋለችና። በሥልጣን ባልጋችሁ፣ በገንዘብ ታውራችሁ፣ በጥጋብ ደንቁራችሁ፤ ህሊና ላጣችሁ፣ ማየት ለተሳናችሁ፣ ብሶት አንስማ ላላችሁ "ጊዜ የእኛ ነው" ብላችሁ የምታደርሱት ግፍና በደል ትውልድ ቢተካ እንኳ ልትጠየቁ የምትችሉበት ጊዜ ገደብ እንደሌለው ማስተዋሉን ይስጣችሁ፣ ይህ ትምህርት ይሁናችሁ እንላለን። በእናንተ ግፍና ጭካኔ ልጆቻችሁን አንገት አታስደፉ።

በጎጃም ክፍለ ሀገር ደብረማርቆስ ከተማ በ1969/70/71/72 የደርግ ቀይ ሽብር ዘመቻ ዋና ተዋናይ የነበረው ነፍሰ ገዳይ የደርግ አባል የ፻ አለቃ እሸቱ ዓለሙ በቁጥጥር ሥር መዋሉን የዛሬ ሁለት ዓመት ባወጣነው ጋዜጣዊ መግለጫ መዘገባችን ይታወሳል።

የዚህ ወንጀለኛ የፍርድ ሂደት በኔዘርላንድ ዘ ሄግ ፍርድ ቤት ከሰኞ October 02, 2017 ጀምሮ በመቶ አለቃ እሸቱ ዓለሙ ላይ የምስክርነት ቃላቸውን እየሰጡ በነበሩት በሕይወት ከተረፉ የጊዜው ሰለባዎችና ቤተሰብ አባላትን በማድመጥ ተካሂዷል።

የ63 ዓመት ዕድሜ እንደሆነ የተነገረው እሸቱ ዓለሙ በጎጃም ደብረማርቆስ በመቶዎች የሚቆጠሩ ወጣቶችን በደርግ ቀይ ሽብር ዘመን የፈጀ አረመኔ ነበር። የ፻ አለቃ እሸቱ ዓለሙ አሁን ባለው አገዛዝ በሌለበት የሞት ፍርድ የተፈረደበት ወንጀለኛ ነው።

"ያ ትውልድ ተቋም" በደርግ ቀይ ሽብርና ግድያ ሰለባ የሆኑ ወገኖችን ስምና ምስል የያዘው ድረ ገፃችንን (www.yatewlid.com, www.yatewlid.org) በመጎብኘት መመልከት እንደምትችሉ እየገለጽን በዚህ ዕትማችን የመቶ አለቃ እሸቱ ዓለሙን የፍርድ ሂደት ዜና በማስመልከት በጎጃም ክ/ሀገር የኢሕአፓ አባላት ናችሁ በመባልና በሌላም ከተገደሉትና በድረ ገጻችን ከዘገብናቸው 290 የጎጃም ወገኖቻችን መካከል መቶ አለቃ እሸቱ ዓለሙ የተሳተፈበትንና የተከሰሰበትን የ75 ወጣቶች ግድያ ጨምሮ በደብረ ማርቆስ ከተማ የተጨፈጨፉ 131 ወገኖቻችን ስም ዝርዝር ለመታሰቢያነት በመጨረሻው ገፃችን አውጥተናል (አባሪ 1 ይመልከቱ)። እናንተ ሰማዕታት ዛሬ ስማችሁ ከመቃብር በላይ ከፍ ብሏል እንላቸዋለን። ታሪካችሁ በጨለማ እንዳሉ ክዋክብት የሚያበራበት ጊዜው እሩቅ እንደማይሆን ተስፋ አለን።

በተጨማሪ ደም ያዘለ ዶሴ፤ ልዩ አቃቤ ሕግ ጽ/ቤት ዘገባ ጥር 2002 ዓ.ም. አዲስ አበባ፤ ከአገኘነው የ፻ አለቃ እሸቱ ዓለሙ የወንጀል ዘገባ የቀነጨብነውንና ዛሬ በድርጊቱ ምንም እንደሌለበት ሁነው መጽሐፍ ለሚያስነብቡን የደርግ ቀይ ሽብር አመራሮች ክህደትና ማንነትን ሕዝብና አንባቢ ይረዳው ዘንድ ቀጥሎ በማቅረብ ጽሁፋችንን እንቋጫለን።

ቴሌግራም 28.5.70 ከም/መ/አለቃ እሸቱ ዓለሙ ለብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ እንዲያውቁት ለሻምበል ፍቅረስላሴ፤ ፀረ-ሕዝቦችን ለመመንጠር በኦፕሬሽን ላይ ነኝ:: . . . በዛሬው ዕለት በ7 ሰዓት ሁለት የፖሊስ አባሎች አንድ ሻምበል ሌላው የአስር አለቃ . . . ላይ እርምጃ ተወስዷል:: . . . ሁለቱም ተገድለዋል:: ሴሚናሩና ምንጠራው አሁንም እንደቀጠለ ነው እስከ ነገ ድረስ ሁሉም ተይዘው እስካለቁ ድረስ ኦፕሬሽኑ ይቀጥላል:: ም/መ/አ እሸቱ ዓለሙ

በፋይል ይቀመጥ:: ፊርማ ሻምበል ፍቅረስላሴ ወግደረስ 4.6.70[114]

ለጎጃም ክፍለሀገር ወህኒ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት ደብረማርቆስ:- ስማቸው ከዚህ ጋር ተያይዞ በተላከልዎት ዝርዝር የተገለፀው 80 /ሰማንያ/ ፀረ-አብዮተኞች ፀረ-አብዮት ድርጊታቸው በጣም ከፍተኛ በመሆኑ አብዮታዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ሆኖ አፈፃፀሙ እንዲገለፅ ያደርጉ ዘንድ አስታውቃለሁ 8/12/70 ም/መ/አ እሸቱ ዓለሙ የክፍለሀገሩ ቋሚ የደርግ አባል፣

ለጓድ መቶ አለቃ እሸቱ ዓለሙ
የጎጃም ክፍለሀገር ቋሚ የደርግ አባል ደብረማርቆስ[115]

በ8/12/70 በቁጥር 448/4/11 በተፃፈልን ትዕዛዝ መሰረት 71 ፀረ-አብዮተኞች አብዮታዊ እርምጃ ሲወሰድባቸው፣ ሶስቱ ቀደም ሲል ከወህኒ ቤት፣ ሲያመልጡ የተገደሉ አንድ በዚሁ ቀን የጠፋ፣ አምስቱ ግን በመተከል አውራጃ ወህኒ ቤት የሚገኙ መሆኑን እየገለፅን ዝርዝሩን በዚህ ደብዳቤ አማካይነት መላካችንን እናሳስባለን:: ኢትዮጵያ ትቅደም ወንድምዬ ኃይሌ ኮለኔል የጎጃም ክፍለሀገሮች ወህኒ ቤቶች ዋና አስተዳዳሪ:-[116]

አባሪ 1. በጎጃም ክ/ሀ ደብረማርቆስ በ1969/70 በደርግ ቀይ ሽብር የተረሸኑ

| ጎጃም ደብረማርቆስ በ1969/70 በደርግ ቀይ ሽብር የተገደሉ | | | |
|---|---|---|---|
| ተራ ቁ. | ስም ከነአባት | የተገደሉበት ቀን | መግለጫ |
| 1 | አለነ ውበቱ | | |
| 2 | አበበ | | |
| 3 | አብይ ዘላለም | | |
| 4 | ዓለሙ ደስታ | | |
| 5 | አያሌው ከበደ | | |
| 6 | አዳነ ቢራራ | | |
| 7 | አበባው ተድላ ዓለሙ | | መምህር: አ.አ |
| 8 | ዓለማየሁ ደሴ እምሩ | | አአዩ |
| 9 | አሰፋ ጥሩነህ | | |
| 10 | ዓለማየሁ ተመስገን አሥራት | 1970 | |
| 11 | አበበ አያሌው ለማ | | |
| 12 | አላምረው ገደፋው ተበጀ | | |
| 13 | አህመድ ነጋሽ ሁሴን | | |
| 14 | ዓለማየሁ ምትኩ ኃይሌ | | |
| 15 | አንማው ባሳዝነው ስመኝ | | |
| 16 | አጥናፉ ስንሻው ሙሉነህ | | |
| 17 | አባትሁን አዳነ ትዕዛዙ | | |
| 18 | አምሳሉ በላቸው በየነ | | |
| 19 | አሰፋ ኃይሉ ይመር | | |
| 20 | አበባው ተድላ ዓለሙ | | |
| 21 | አህመድ ጌታሁን ዓለሙ | | |
| 22 | ዓለማየሁ ደሴ እምሩ | | |
| 23 | አሰፋ ባይነሳኝ ከበደ | | |
| 24 | አእምሮ በላይ ደስታ | | |
| 25 | አበበ በላይ ትርፌ | | |
| 26 | ዓለማየሁ አረጋ ካሣ | | |
| 27 | አበባው ገላዬ ወንድም | | |
| 28 | በላቸው ዓለሙ በዛብህ | | |
| 29 | በላይ ላቀው በየነ | | |
| 30 | ቢያምረኝ ደረሰ በላቸው | | |
| 31 | በዛ ንጉሴ አስረስ | | |
| 32 | ብርሃኑ ወርቅነህ አብዲ | | |
| 33 | ብርሌ አንበሽ በማንጃ | | |
| 34 | በላይ ቱኮ ወልዴ | | |
| 35 | ብዙዓለም ደምሴ ወ/ሩፋኤል | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 36 | ብርሃኑ እረሊ ሙለታ | | |
| 37 | በላቸው አደመ | | |
| 38 | በላይ ትኬ ተወልደ | | |
| 39 | ጫኔ በዛብህ አዳሙ | | |
| 40 | ደሳለኝ አስናቀ ጀምበሬ | | |
| 41 | ደሜ ፀሐይ አብርሃም | | |
| 42 | ዳዊት ዘውዴ ወርቁ | | |
| 43 | ደግአረገ ዓለሜ አየለ | | |
| 44 | ደስታ ተሰማ መሸሻ | | |
| 45 | ድልነሳሁ አየለ በላይ | | |
| 46 | ደሳለኝ ጉዲሳ ደሜ | | ከወህኒ ቤት ሲያመልጡ የተገደለ |
| 47 | እስጢፋኖስ ገ/መስቀል አትሾም | | |
| 48 | እጅጋየሁ ገ/መድህን ናደው | | |
| 49 | ኤፍሬም አርአያ መሰረት | | |
| 50 | እንግዳወርቅ ጥላሁን ወርቅነህ | | |
| 51 | እውነቱ አበበ ቸኮል | | |
| 52 | እንዳወቀ ጥላሁን ወርቅነህ | | |
| 53 | ፈትሃልዴን ጀብሪል ሰይድ | | |
| 54 | ፈጠነች ዘለቀ ተገኝ | | |
| 55 | ፈጠነ ሀብቴ ወልደህፃን | | |
| 56 | ፈረደ ሁነኛው ንገሴ | | |
| 57 | ጌታሁን ተኬ | | ከ01ቀ05 |
| 58 | ጌትነት ደስይበለው | | |
| 59 | ግርማ ዓይናለም ደስታ | | |
| 60 | ገረመው ዋሴ አገኘ | | |
| 61 | ኃይሉ ውብሸት ወርቅነህ | | |
| 62 | ኃይሉ ካሣ ጎንፋ | | |
| 63 | ኃይሉ ገላዬ ወንድም | | |
| 64 | ካሣ አሰፋ ነጋሽ | | |
| 65 | ካሱ መኮንን ዘሪሁን | | |
| 66 | ቀረብህ ታፈረ ዓለሙ | | |
| 67 | ክንዴ ገበየሁ አሣየ | | |
| 68 | ካሳ አሰፋ ነጋሽ | | |
| 69 | ለገሰ ሰይድ አብዲ | | |
| 70 | ላቃቸው አባቴነህ ብርሃኑ | | |
| 71 | መላኩ ወ/ተንሳይ | | |
| 72 | ሙሴ ብርሃኔ | | |
| 73 | ሚካኤል ከበደ | | |
| 74 | ሙሉካሳ ደምለው መለሰ | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 75 | ሙሴ በያን | | |
| 76 | ሙሉጌታ ብዙነህ ደርሰ | | |
| 77 | መሐመድ ሁሴን እሸቱ | | |
| 78 | ሙሉጌታ አስፋው ወ/ጊዮርጊስ | | |
| 79 | መሐሪ ዘሪሁን አዳብ | | |
| 80 | መላኩ ኢተፍ ሞርኪ | | |
| 81 | ሙሉጌታ ተገኝ ሀብቱ | | |
| 82 | ማዘንጊያ ደሴ ተገኝ | | |
| 83 | ሙሉ ካሣ ደምለው | | |
| 84 | ምስክር ጥላሁን ሣህሉ | | |
| 85 | መሐመድ ሀሰን መሐመድ | | |
| 86 | መህሪ ዘርይሁን አደብ | | |
| 87 | መላኩ ይተፋ ሞርኪ | | |
| 88 | ንጋቱ ገብሬ ይኩኖ | | |
| 89 | ንብረት አድማሱ አካሉ | | |
| 90 | ነብዩ መስፍን ዓለማየሁ | | |
| 91 | ሰርጉዓለም ሙሴ | | |
| 92 | ሰፈፌ የሲጋት | | |
| 93 | ሠርጉ ሙሄ ንጉሴ | | |
| 94 | ሰሎሞን ከበደ ጥሩነህ | | |
| 95 | ሥነመንግስት ዘውዴ ሰዋገኘሁ | | |
| 96 | ስመኘው ቢሻው መለሰ | | |
| 97 | ሳሙኤል ሰብስቤ ዘርይሁን | | |
| 98 | ስነመንግስት ዘውዴ ሰውአገኘሁ | | |
| 99 | ሲያምረኝ ደረሰ በላቸው | | |
| 100 | ሰለሞን ጳውሎስ ገብርኤል | | ከወህኒ ቤት ሲያመልጡ የተገደለ |
| 101 | ሽታሁን መላኩ ንጉሴ | | |
| 102 | ሽመልስ ደስታ ድንበሩ | | |
| 103 | ሽምሱ ጀብራል ደስታ | | |
| 104 | ሽፈራው አቡኔ አድጉ | | |
| 105 | ሺመልስ ደስታ ጀምበሩ | | |
| 106 | ታመነ ተመስጌን | | |
| 107 | ተመስገን ተረፈ ድንቂ | | |
| 108 | ታደሰ ኢያሌው ያለው | | |
| 109 | ተፈራ መንግሥቱ ጥምቀት | | |
| 110 | ተፈራ ሲሳይ አለምነህ | | |
| 111 | ታደለ ያደታ ገልሞ | | |
| 112 | ተመስገን አሥራት ካሣ | | |
| 113 | ተክለገነት ሐረገወይን ፀዳሉ | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 114 | ተሻገር መሰሉ ዓለሙ | | |
| 115 | ታምራት ለገሰ ታፈረ | | |
| 116 | ተስፋዬ ደሴ ደጉ | | |
| 117 | ተገኝ ተስፋዬ ገለታ | | |
| 118 | ተሰማ ኃይሉ ጀምበር | | |
| 119 | ትኩዬ ልኝለም ወልዱ | | |
| 120 | ቲሣ በዳሳ ሙጫ | | |
| 121 | ታደሰ ገበየሁ ወ/ማሪያም | | |
| 122 | ጣሰው መሪ ማታጉድ | 1971 | |
| 123 | ቲሳ በደሌ ሜጫ | | |
| 124 | ታደሰ እንግዳ ብርሌ | | ከወህኒ ቤት ሲያመልጡ የተገደለ |
| 125 | ወንድሜነህ ጫኔ ተገኝ | | |
| 126 | ወረታ ሞገስ ወ/ጊዮርጊስ | | |
| 127 | ወልደትንሣኤ ጥላሁን | | |
| 128 | ይርጋ ካሣ (አሰግደው) | | |
| 129 | የውልሰው እንደኛነው ባለህ | | |
| 130 | ዘይኑ እድሪስ ወሌ | | |
| 131 | ዘገየ መስፍን ጎበና | | |
| | | | |

«ያ ትውልድ ተቋም» ለመረጃ ምንጭነት!
የተጐዱ ወገኖችን ለመርዳት!
ለያ ትውልድ መታሰቢያነት!

የያ ትውልድ ታሪክ ህያው ነው!!!

ጥቅምት 28 ቀን 2010 ዓ.ም. (October 7, 2017)

**ዋቢ ማጣቀሻና መረጃዎች፣**

- ደም ያዘለ ዶሴ ጥር 2002 ዓ.ም.፥ የልዩ አቃቤ ሕግ ጽ/ቤት፤ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
- አዲስ ዘመን ዕለታዊ ጋዜጣ የወቅቱ ዕትሞች
- ያ ትውልድ ጋዜጣዊ መግለጫ፡ ጥቅምት 8 ቀን 2008 ዓ.ም.
- ያ ትውልድ ድረ ገጽ

**«ያ ትውልድ ተቋም»**

- ኢሜል : yatewlid@yahoo.com, yatewlid@gmail.com,
- ድረ ገጽ : http://www.yatewlid.com , http://www.yatewlid.org
- ምስለ ገጽ : yatewlid